# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

# Ethiopian People´s Revolutionary Party (EPRP)

**የካቲት 2 ቀን 2004 ዓ. ም**

## ኢሕአፓ አሁንም ከኢትዮጵያ ሙስሊም ወገኖቻችን ጎን መቆሙን ያረጋግጣል።

የወያኔ ቡድን ሥልጣኑን ከጨበጠበት ጊዜ ጀምሮ ተደላድሎ ለመቀጠል እንዲያስችለው በተለያዩ የሃይማኖት ተቋማት ላይ መዝመቱ ይታወቃል። ባጠቃላይ የሃይማኖት ተከታዮችን መብት እየረገጠ፤ የሃይማኖት አባቶችን በተለያዩ ተጽእኖዎች የሱ ታማኝና ተከታይ እንዲሆኑ ለማድረግ፤ የሃይማኖት ተቋማቱን ደግሞ ለፖለቲካ መጠቀሚያነት ለመገልገል ሲጥር መቆዮቱ በገሃድ ሲታይ የቆየ ነው። በቅርቡ በብዙሃኑ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ላይ ባደረገው የመብት ጥሰቶች ከፍተኛ ተቃውሞ ያጋጠመው ሲሆን ይህንን ተቃውሞ ለመግታት አሁንም ከፍተኛ የመከፋፈል ተንኮል እያካሄደ ይገኛል።

ገና ሥልጣን ሲይዝ በብሔር መብት ስም የጀመረው የከፋፋይነት መርዝ እየረከሰበት፤ ተቀባይነት እያጣ ሲመጣ አሁን ደግሞ በሃይማኖት ተቋማት ውስጥ ጣልቃ በመግባት የክፍፍል ስልቱን በአዲስ መልክ ቢቀጥልበትም፤ ይህንን በብርቱ የሚቃወሙ የአወሊያና  የሌሎችም ትምህርት ቤቶች እስላም ተማሪዎችና ወጣቶች መብታችውን ለማስከበር እንዳለፈው ትውልድ ሁሉ ከፍተኛ ተቃውሞ ሲያደርጉ ቆይተዋል። የተማሪዎችንና ባጠቃላይም የሙስሊሙ ወገናችንን ጥያቄዎች በአግባቡ በመመለስ ፋንታ የወያኔ ቡድን የአፈና ተግባሩን አጠናክሮ እየገፋበት ነው። መምህራኖቻቸው ያላግባብ ከሥራቸው ተባረዋል፤ አንዳንድ የእስልምና ምሁራንም በተለያዩ ቦታዎች ታስረዋል። ይህንን አስከፊና መብት ረጋጭ የወያኔን እርምጃ ዝም ብለው መመልከት ያልቻሉት የአወሊያና እንዲሁም የሌሎች ትምህርት ቤቶች እስላም ተማሪዎች የተቃውሞ እንቅስቃሴ በተጠናከረ መልክ በመካሄድ ላይ ይገኛል።

ኢሕአፓ እስከዛሬ ድረስ መብቱ ተገፎ ከቆየውና አሁንም ለመብቱ  እየታገለ ካለው ከሙስሊም ኢትዮጵያዊ ወገኖቹ ጎን አብሮ እንደሚሰለፍ በዚህ አጋጣሚ አፅንዖት በተሞላበት ሁናቴ ያረጋግጣል።

የኢትዮጵያ ሙስሊም ወገኖቻችን መብት በማያሻማ መንገድ ሊከበር የሚችለው የሁሉም ኢትዮጵያዊያንን መብት የሚያስከብር ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በሕዝቡ የሥልጣን ምንጭነት ሲመሠረት ስለሆነ፤ ይህንን ሥርዓት ለመመሥረት ለሚደረገው እልህ አስጨራሽ ትግል በተጨባጭ ትብብር ትግሉን ማጠናከር ከመቼውም ጊዜ በላይ አሁን ነው እያልን የትግልና የትብብር ጥሪያችንን እናቀርባለን። መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በነፃ ድርጅቱ ዙሪያ በመሰለፍና የጋራ ትግሉን በማጠናከር የመብቱ ባለቤት እንደሚሆን አንጠራጠርም!

እናቸንፋለን!

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail: ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France